

# ቀን ሦስት፡-የብስንና ውሃን ለየ፤ ምድርም ባለዘፍ ፍሬ አበቀለች [ዘፍ1 9-13]



"እግዚአብሔርም፡- ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፥ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውኃ መከማቻውንም ባሕር አለው እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም፡- ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ሦስተኛ ቀን።" [ዘፍ1 9-13]



- † እስካሁን ከምድር በላይ ብርሃንን፥ ጠፈርንም ፈጥሯል። አሁን ደግሞ የሰው ማደሪያ ልትሆን ወዳሰባት ምድር ዝግጅት እያደረገ ነው፡፡
- † ከሰማይ በታች ያለውን ውሃ በመሰብሰብ የብሱን ገልጦታል፡፡
- † የብሱንም ባለ ፍሬ ዛፍ እንዲሰጥ አድርጓል፤
- † ባዶ የነበረችው ምድር አሁን የብስ ተገልጦባት፤ ሣርንና ቡቃያን፥ ፍሬንም የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አብቅላለች።



ሚስጢሩ

- † በውሃ የተመሰለው ይህ አሮጌ የሰው ሕይወት [ራእ17 15] ፤ ለእግዚአብሔር መንፈሳዊ ፍሬን ማፍራት አይችልም፡፡ ከዚህ አሮጌ ማንነት የሚወጣው አዲስ ሕይወት ግን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ ፍሬ የሚያፈራ እርሱ መሆኑን ያሳያል፡፡

"እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።"[ዮሃ15 5]

"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።" [ገላ5 22]

ሚስጢሩ ....

†እግዚአብሔር ከላይ ሲናገር የብሱ እንደተለየ፤ በኋላም ፍሬን እንደሰጠ፤....በፍሬ አልባ ባዶ መሬት የተመሰለው በአዳም መተላለፍ ከእግዚአብሔር ተለይቶ በመንፈሱ የሞተ ሰው፤ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተነገረውን የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ምስክርነት ሰምቶ ሲያምንበት መንፈሳዊ ፍሬን የማፍራት ብቃት ይኖረዋልና፡፡



ሚስጢሩ ....

†ይኸውም "እናንተ የእግዚብሔር እርሻ ናችሁ፡፡" [1ቆሮ3$^9$] እንደሚለዉ፤ በአማኙ ውስጥ ከሚያድረው ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ፥ ፍሬን በርሱ ከሚያፈራውም ከክርስቶስ እንደሆነ እናያለን፡፡ በዚህም ከውሃ በመለየት ፍሬ ያፈራው የብስ፤ በክርስቶስ ያለ አዲሱን ሰው የሚያሳይ እንደሆነ እናያለን፡፡



እግዚብሔርን ደስ ሊያሰኝ የሚችል ፍሬ የሚያፈራዉ፣ አዳማዊዉ ማንነታችን ሳይሆን፣ ከማይጠፋዉ ዘር የተወለድንበት፣ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውና የለበስነዉ አዲሱ ሰው ብቻ ነዉና።



ከዚህ እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ ከተፈጠረውና ከለበስነዉ አዲሱ ሰው የተነሳ..........

እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል። [1ጴጥ2$^{9-10}$]

...........እንደተባለልን እንገነዘባለን፡፡

በዚህም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ስንቀበል በስሙም ስናምን ከእግዚብሔር እንወለዳለን፣ በመወለዳችን የምንለብሰዉ አዲሱ ሰዋችን በእግዚብሔር ምሳሌ የተፈጠረ ነዉና፣ እግዚብሔርን ደስ ሊያሰኝ የሚችል ፍሬ የሚያፈራዉ እርሱ ብቻ እንደሆነ እናያለን፡፡



ስለዚህም ምክንያት የጽድቅን ሥራ ለመስራት በጉልበታችን የምንታገልበት ሳይሆን፣ መዳናችንን ባገኘንበት የእግዚብሔር መንፈስ ኃይል ክርስቶስ በኛ ዉስጥ የሚኖረዉ የርሱ ሕይወት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

.... መጽሐፍ ቅዱስ በማያሻማ መንገድ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና። [ፊል$2^{13}$] ይላልና!



በሌላ ቦታም እንዲሁ...

ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።

[ፊል$4^{13}$] ይላል!



አሁንም በሌላ ቦታም...

በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤

[ፊል$1^{6}$-ሉቃ$14^{27-32}$] ይላል!

እንዲሁ መምህረ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ...

"እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። <u>ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና</u> በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።" [ዮሃ15[5]]

ያለዉንም አንዘነጋዉም!!!



"እግዚአብሔርም፦ ከሰማይ በታች ያለው ውኃ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፥ የብሱም ይገለጥ አለ እንዲሁም ሆነ። እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውኃ መከማቻውንም ባሕር አለው እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም፦ ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል አለ እንዲሁም ሆነ። ምድርም ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን እንደ ወገኑ ዘሩም ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን እንደ ወገኑ አበቀለች። እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደ ሆነ አየ። ማታም ሆነ ጥዋትም ሆነ፥ ሦስተኛ ቀን።" [ዘፍ1[9-13]]